## እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

### ማስታወቂያ

### የሕቶች ፕሮግራም

አጠቃላይ የሕቶች ፕሮግራም ዛሬ ከአገልግሎት በኋላ ስለሚኖር እህቶች ሁሉ እንድትገኙ አስተባባሪዎች በጌታ ፍቅር ይጠይቃሉ። ጌታ ይባርካችሁ!

### አጠቃላይ ስብሰባ

በMarch 18 አመታዊ ሪፓርት የሚቀርብበትና እቅዶች ላይ የምንነጋገርበት ስብሰባ ስለሚኖር የቤተ ክርስቲያን አባላት ሁሉ እንድንገኝ ችማግሌዎች ያሳስባሉ።

### G&B TV Ministry ድጋፍ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም

የG&B TV Ministry የገንዘብ ድጋፍ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም በMarch 24 (2-5pm) በብርሃነ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ስለሚኖር አባካችሁ ተገኝተን ይህንን አገልግሎት እንደግፍ።

### የአርብ ፕሮግራም

ዘወትር አርብ በሚኖረን የጸሎትና የቃል ፕሮግራም ላይ በመገኘት እንድንካፈል ቤተ ክርስቲያን ታበረታታለች።

### የሕንጻ ፈንድ

የሕንጻ ፕሮግራማችን ላይ አሁንም ተሳትፎአችን እንዲቀጥል ቤተ ክርስቲያን ታበረታታለች።

"ወደ ውጭም አውጥቶ፡- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? ኣላቸው።
እነርሱም፡- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ **Yeec.org App** ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-
773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0194 (ወ/ም አያሌው)
773-910-0485 (ወ/ም ፒተር)
773-961-5332 (ወ/ም ጌቱ)
773-739-0437 (ወ/ም ሰለሞን)

### መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

---

# የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን

# Chicago Yemsrach Evangelical Church

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10




## "የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው ..."

(ማሳሌ 9፡10)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

www.yeec.org

መደበኛ ፕሮግራሞች
እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

**March 11, 2018** | **መጋቢት 2፣ 2010 ዓ.ም.**

# የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት መሪ................ | ወንድም ዘሪሁን ዳዊት |
| አምልኮ...................... | የቤተክርስቲያን አምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም ጴጥሮስ መኩሪያ |
| ቃል ............. | ወንድም ጻደቀ ጴጥሮስ |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

## <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

"በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ።"

(ፊል. 4:6)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሐሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ሰለሞን ወመነ | ቅዳሜ | 549 Sheridan Rd., Apt. 3, Evanston, IL 60202 |

# መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

**እግዚአብሔርን የሚፈራ ሌላ አይፈራም!**

ከ2013 በጸጋው ታደለ የሚባል ወንድም በአትላንታ ከተማ ከሚገኘው ሞርሃውስ ኮሌጅ 3.99 በማምጣት በኮምፐተር ሳይንስና በሂሳብ ትምህርት ተመረቀ። ይህን እጅግ በጣም ከፍተኛ ውጤት በማምጣቱም በወቅቱ ለምሩቃኑ ንግግር ያደረጉት ፕሬዝዳንት ባራክ ኦባማ የተመራቂውን ስምና ትክለ-ሰውነት ከራሳቸው ጋር በማመሳሰል አመስግነውት ነበር። ወንድም በጸጋውም በእለቱ ከፕሬዝዳንቱ እጅ የክብር ሽልማት ተቀብሏል። የበጸጋው አኩሪ ውጤት በበርካታ የመገናኛ ብዙኋን የተዘገበ ሲሆን በወቅቱ ከቀሩቡለት ጥያቄዎች መካከል "ፕሬዝዳቱን ስታገኝ ፍረሃት አልተሰማህም ወይ" የሚል ነበር። በጸጋው ሲመልስ "እኔ አስቀድሜ በመለዳ ሰማይና ምድርን በፈጠረው ንጉስ ፊት ቀርቤ ስለምወጣ ሌላ ንጉስ አያስፈራኝም" የሚል ነበር።

መጽሐፍ ቅዱስ "የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው ቅዱሱንም ማወቅ ማስተዋል ነው" ይለናል። (ማሳሌ 9:10) በእርግጥም ማንም ጥበበኛ ነኝ የሚል እግዚአብሔርን የማይፈራ ቢኖር የርሱ ጥበብ ከንቱ ነው። ጥበብ እራሷ ጀመሪዋ እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔርን መፍራት ማለት ለእግዚአብሔር የሚገባውን ክብር መስጠትና ትእዛዙን መጠበቅ ነው። እግዚአብሔር የሚፈራው ከፍቅሩና ከአባትነቱ የተነሳ ነው። የተመሰገነ አባት እንደሚፈራና እንደሚከበር ሁሉ እግዚአብሔር እንዲሁ ሊፈራና ሊከበር ይገባዋል። እግዚአብሔር ህዝቡን "እናንተ ስሜን የምታቃልሉ ካህናት ሆይ፥ ልጅ አባቱን፥ ባሪያም ጌታውን ያከብራል እኔስ አባት ከሆንሁ ክብሬ ወዴት አለ? ጌታስ ከሆንሁ መፈራቴ ወዴት አለ?" በማለት የጠይቃል። እግዚአብሔር ህዝቡ እንደ አባትነቱና ጌትነቱ እንዲያከብረው እና እንዲፈራው ይፈልጋል።

ወገኖቼ፡- በእርግጥም ንጉሱን እግዚአብሔርን የሚፈራ ሌላ ማንንም አይፈራም። መጀመሪያውና መጨረሻው እርሱ ነው። እርሱ የሁሉ የበላይና ገዢ ነው። ሞት ድል የተነሳው በእርሱ ነው። እግዚአብሔርን ከፈራን ሰው አይስፈራንም፤ እግዚአብሔርን ከፈራን ያለንበት ሁኔታ አያስፈራንም። እርሱን ከፈራን ቀና ብለን እንሄዳለን። ምክንያቱም እርሱን ከፈራን እርሱ ከኛ ጋር ይሆናል። እርሱ ከኛ ጋር ከሆነ ማንም ሊቃወመን አይችልም። እርሱን ብቻ ስንፈራ ዳዊት እንደዘመረው "እግዚአብሔር ረዳቴ ነው፥ አልፈራም ሰው ምን ያደርገኛል?" እንላለን። እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው በእርሱ ጥበቃ ውስጥ ያድራል። ብዙ አስፈሪ ነገሮች በዙሪያው ቢሆኑም እርሱ ግን በእግዚአብሔር ላይ በመታመን ይወጣል፣ ይገባል። የተጣለና ለጠላት አልፎ የሚሰጥ አይሆንም። በእርግጥም በእግዚአብሔር ጥበቃ ውስጥ ተማምኖ ይኖራል። በወቅቱ ነፋስ እየተፍገመገመ ሰላሙ አይወሰድም። ማንኛውንም ጉዳይ የበላይ ወደ ሆነው አምላኩ ያቀርባል ነገር ግን አይታወክም። ምክንያቱም በእርሱ ዘንድ መፍተሔ እንዳለ ያውቃል። አሜን!